# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 342 ህዳር 19 2007 ገጽ

ህወሓት በገሀድ በጠላትነት የፈረጃቸው የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣ መምህራንና ሠራተኞች ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ በአጽንኦት እንዲመለከቱ ግንቦት 7፣ የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያሳስባል። ትውልድንም የትምህርት ሥርዓቱንም የማዳን ግንባር ቀደም ኃላፊነት በተማሪዎችና በመምህራን የወደቀ ሸክም ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በሰሜን ጎንደር ዞን የተቀሰቀሰው ግጭት የንጹሃን ኢትዮጵያውያንን ህይወት እየቀጠፈ መቀጠሉ ታወቀ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሰሜን ጎንደር ዞን በእርሻ ስራ ላይ በቀን ሰራተኝነት ተቀጥረው የሚሰሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን በጎጥ በማቧደን እርስ በእርስ እንዲጋጩና እንዲገዳደሉ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ምንጮቻችን አመልክቱ። በዞኑ በኢንቨስትመንት ስም ንጹሃን ዜጎችን በግፍ በማፈናቀል ለም መሬቶችንን ተቆጣጥረው የሚገኙት የጉጅሌው ሹማምንቶችና ሸርካ ቅጥረኛ ባለሃብቶች ከጉልበታቸው ጋር ተመጣጣኝ ባልሆነ ክፍያ በቀን ሰራተኝነት ቀጥረው የሚያሰሯቸውን በተለይ ከአማራ ክልል ጎንደር፤ ጎጃም፤ ሸዋ እና ወሎ የመጡ ሰራተኞችን በጎጥ በመከፋፈል እርስ በርስ እንዲገዳደሉና እንዲጨራረሱ እያደረጉ ሲሆን በእስካሁኑ የአገዛዙ እኩይ ሴራ በርካቶች መገደላቸውንና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩት ደግሞ የሰሩበትን የጉልበታቸውን ዋጋ ሳይሰበስቡ አካባቢውን ለቀው ነፍሴ አውጭኝ ሽሽት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ግጭቱን ተከትሎ በታች አርማጮ በሰቲት ሁመራ፤ በማይካድራ፤ በመተማና ሽዲ እንዲሁም በሌሎችም አጎራባች ከተሞች ከፍተኛ ውጥረት ነግሶ እንደሚገኝ ምንጮቻችንን ጠቁመዋል። በዚህ በያዝነው ሳምንት ብቻ ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ በርካታ ሬሳዎች ከየ ከተማዎቹ ሲለቀሙ እንደነበር የጠቆሙን ምንጮቻችንን ግጭቱ ከቀን ቀን እየተካረረና እየተስፋፋ መሄዱ የዞኑን ነዋሪዎች ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ከቷቸው እንደሚገኝ አመልክተዋል።

## የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ጦሩን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እያንቀሳቀሰ መሆኑ ታወቀ

ከፍተኛ አለመረጋጋትና ውጥረት ውስጥ የሚገኘው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከፍተኛ ፍጥነት እየተደራጁና እየተጠናከሩ የመጡት የነፃነት ሃይሎች ጥቃት ሊፈጽሙ ይችላሉ በሚል ስጋት በመወጠሩ ጦሩን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እያንቀሳቀሰ መሆኑን የውስጥ ምንጯችን አመልክቷል። አገዛዙ ለብዙ ጊዜያት በማሃል አገር ሰፍረው የቆዩትን የመከላከያ ሰራዊት አባላት ሳይቀር ወደ ሁመራና ሌሎችም የሰሜን ኢትዮጵያ የድንበር አካባቢዎች በስፋት እያሰማራ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝን በጠመንጃ ለመፋለምና ከስልጣን ለማውረድ በረሃ የከተቱ የነፃነት ሃይሎችን ወጣቶችና ጎልማሶች እንዲሁም በአገዛዙ ስር ተቀጠረው ይሰሩ የነበሩ የመከላከያ ሰራዊት፤ የፖሊስና ሚሊሻ አባላትን ጨምሮ አገዛዙን በመክዳት ድንበር እያቋረጡ በጠረፍ በኩል ያሉ ሃይሎችን በስፋት እየተቀላቀሉ መሆኑ አገዛዙን ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ጥሎት እንደሚገኝም ምንጯችን ያደረሰን መረጃ ያሳያል። በቅርቡ በጎንደር አካባቢ ከ 40 በላይ የአካባቢው ወጣቶችን ጨምሮ ፖሊስና ሚሊሻዎች የነፃነት ሃይሎችን ለመቀላቀል በረሃ መክተታቸው የተዘገበ ሲሆን ከመከላከያ ሰራዊት አባላት ከባድሜ ግንባር ብቻ ከ 107 ያላነሱ ወታደሮች ከድተው ወደ ጠረፍ በመሻገር የነፃነት ሃይሎችን መቀላቀላቸው አይዘነጋም። ከባድሜ አካባቢ ሲያጎ በተባለው ቦታ ላይ የሰፈሩ 60 የ 33ኛ ክፍለ ጦር አባላት በአንድ ሌሊት ሰራዊቱን ጥለው መጥፋታቸው መዘገቡ ይታወሳል። አገዛዙ የመከላከያ ሰራዊቱን መክዳት ተከትሎ በተለያዩ ጊዜያት አዲስ አባላትን ለመመልመል ማስታወቂያ በተደጋጋሚ ቢያወጣም ተመዝጋቢ በማጣቱ ነባርና ተቀናሽ የሰራዊት አባላትን ዳግም ሰራዊቱን እንዲቀላቀሉ ሽንገላ ቢይዝም አለመሳካቱ ይታወቃል።

## የአዲስ አበባ ተዋሳኝ ከተማ የሆነችው ለገጣፎ በተቃውሞ እየተናጠች መሆኗ ታወቀ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በለገጣፎ ከተማ ከ 3,000 ሺህ በላይ ቤቶች እንዲፈርሱ ትዕዛዝ ማሳለፉን ተከትሎ ነዋሪዎች ለተቃውሞ አደባባይ መውጣታቸውን ምንጮቻችን አመለከተዋል። በከተማዋ ሹማምንቶች የሚመራው የአገዛዙ ቤት አፍራሽ ግብረ ሃይል ከበላይ ጉጅሌዎች የወረደውን ትዕዛዝ በመቀበል በየካ ሰዴን ወረዳ የሚገኙት የጉራ፣ ሰፈራ፣ ድሬ፣ ዳሌ እና ቀርሳ በሚባሉ አካባቢዎች ውስጥ የሚገኙ ከ 3000 ሺህ በላይ እንዲፈርሱ ህገ ወጥ ትዕዛዝ የተላለፈባቸው ቤቶች ላይ ምልክት ማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል። በጉጅሌዎቹ የተላለፈው ትዕዛዝ ከ 32,000 ሺህ በላይ ህጋዊ ነዋሪዎችን ቤት አልባ እንደሚያደርግ ምንጮቻችን ተናግረዋል።

ከ 10 አመት በላይ በአካባቢው መኖሪያ ቀልሰው በህጋዊነት የሚኖሩት ነዋሪዎቹ ካሳለፍነው ቅዳሜ ህዳር 13 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በጉጅሌዎቹ የተላለፈውን ህገ ወጥ ትዕዛዝ በመቃወም በከተማው በመሰባሰብ ተቃውሞ ማሰማት መጀመራቸውን ለማወቅ ተችሏል። ይሁን እንጂ የነዋሪዎቹን ችግር ለማዳመጥ ፈቃደኛ ያልሆኑት የለገጣፎ ከተማ ቅጥረኛ ሹማምንቶች በተደጋጋሚ ነዋሪዎቹ ላቀረቡት የእንነጋገር ጥያቄ መልሰ ሊሰጡ አለመቻላቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ነዋሪዎቹ በደል እና ተቃውሟቸውን ለማሰማት ተወካዮችን መርጠው ወደ በላይ የፌደራል ቱባ ጉጅሌዎች መላካቸው ታውቋል።

በለገጣፎ ከተማ የነገሰውን ከባድ የተቃውሞ ትዕይንት ተከትሎ አገዛዙ ልዮ ሃይል ወደ አካባቢው ማንቀሳቀሱንም ለማወቅ ችለናል። በእስካሁኑ ተቃውሞ ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ግለሰቦች እና ለሽምግልና የተመረጡ የኮሜቴ አባላት ለእስር መዳረጋቸውም ታውቋል። የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በመላ አገሪቱ በብዙ ሺዎች የሚገመቱ ዜጎችን ለዘመናት በህጋዊነት ከሚኖሩበት ቤታቸው በማፈናቀል ቤት አላባ በማድረግ ለከፋ ችግር እየዳረጋቸው እንደሚገኝ በተለያዩ ጊዜያት መዘገቡ ይታወሳል። አገዛዙ ዜጎችን በግፍ ከመኖሪያ ቤታቸው በማፈናቀል ቦታቸውን በኢንቨስትመንት ስም ጉጅሌዎቹ ሹማምንቶችን ጨምሮ ቅጥረኛ ባለሃብቶች እየተቀራመቱት እና እየቸበቸቡት እንደሚገኙም ምንጮቻችንን ዋቢ በማድረግ እየተከታተልን መዘገባችን አይዘነጋም።

## ፍርደ ገምድሉ የወያኔ ፍርድ ቤት ከግንቦት 7 ጋር በተያያዘ ለተከሰሱት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ

አሸባሪው የወያኔ አገዛዝ ትንታግ የሆኑትን ወጣት ፖለቲከኞች በሽብር ወንጀል ተካፍለዋል፣ ድርጊቱን ለመፈጸም ተንቀሳቅሰዋል፣ ህዝብን ለአመጽ ቀስቅሰዋል በሚል የፈጠራ ክስ አጎሮ ስቃይ እየፈጸመባቸው ሲሆን የካንጋሮው ፍርድ ቤት አራቱ ወጣት ፓለቲከኞችን እና በተመሳሳይ መዝገብ የተከሰሱት ሌሎች 6 ተከሳሾች ለቀረበባቸው የፈጠራ ክስ መቃወሚያ እንዲያቀርቡ ለታህሳስ 9 ቀን 2007 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱ ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች አገዛዙ በወጣት ፖለቲከኞች ላይ ያቀረበውን የፈጠራ ክስ እያወገዙ መቀጠላቸው ታውቋል። ወጣት ፖለቲከኞቹን ጨምሮ በአገዛዙ የፈጠራ ክስ ሰለባ ሆነው በእስር እየተሰቃዩ የሚገኙትን የህሊና እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አገዛዙ በአስቸኳይ እንዲፈቱ የሚጠይቅ የበይነ መረብ ዘመቻ መከፈቱም የታወቀ ሲሆን በርካታ ኢትዮጵያውያን ዘመቻውን በመደገፍ ፋሽስታዊው አገዛዝ ሁሉንም የህሊና እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈታ አበክረው እየጠየቁ እንደሚገኙ ዘጋቢያች አመልክቷል።

በሌላ ዜና የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ እያደረሰባቸው ያለው ወከባ፤ አፈናና እስር ትግሉ እንደማይቆም የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር አስታወቀ። “ነጻነታችን በእጃችን” ነው የሚለው ትብብሩ፣ ፋሺስታዊው አገዛዝ እየወሰዳቸው ባሉት እርምጃዎች ፈጽሞ ወደኋላ እንደማይል በማሳሰብ እቅዱን በህጋዊ መንገድ ለማስቀጠል እስከ ህይወት መስዋትነት ለመክፈል ያለውን ቁርጠኝነት ገልጿል።

በመጨረሻም አገዛዙ ከአፈና ድርጊቱ እንዲገታና ለቀረበው ህጋዊ የዕውቅና ጥያቄ በአስቸኳይ መልስ እንዲሰጥ የጠየቀው የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር የትግሉ አላማ የመድብለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሆኑን በማመልከት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ለቀጣዩ ትግል የሚቀርበውን ጥሪ በንቃት እንዲከታተሉና ከፓርቲዎች ጎን እንዲቆሙ፣ ትብብሩን ያልተቀላቀሉ ፓርቲዎችም እንዲቀላቀሉ ጥሪ አቅርቧል።

## ተማሪዎች፣ መምህራን እና የተቋማት ፕሬዚዳንቶች ለአመጽ ተነሱ !

ዘረኛውና አምባገነኑ የህወሓት አገዛዝ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ከካድሬ ማሰልጠኛ ማዕከላትነት ለይቶ የማያይ ስለመሆኑ በተቋማቱ ውስጥ የሚደረጉ ተግባራት ማረጋገጫዎች ናቸው። ለዚህ ተግባሩ በሰነድ ደረጃ መቅረብ ከሚችሉት የቅርብ ጊዜ ማስረጃዎች ዋነኛው በህዳር 2007 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋለው "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኢህአዴግ የምርጫ ድል ልማት ሰራዊት ግንባታ አደረጃጀት ማንዋል" የተሰኘው በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ለሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተላለፈው ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ፣ የህወሓት አሳፋሪ የትምህርት ፓሊሲ ባፈጠጠ መልኩ የተገለፀበት፤ የኢፌዴሪ መንግሥት ተብሎ በሚጠራው የህወሓት አገዛዝ ተቋም እና በህወሓት/ኢህአዴግ ፓርቲ መካከል ለይምሰል እንኳን ልዩነት አለመኖሩ በግላጭ የሚታይበት ሰነድ በመሆኑ በዚህ ርዕሰ አንቀሳችን በስፋት ልንዳስሰው ወስነናል።

ሰነዱ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ መርዙን መርጨት የሚጀምረው ገና በመግቢያው ስለማንዋሉ አስፈላጊነት ሲገልጽ ነው። ማንዋሉ "ከምንም በላይ የብጥብጥና የሁከት መንስኤ የሆነውን ተማሪ በኢህአዴግ አመራር አባላት እየታገዙ ለመያዝ የሚያስችል ነው" በማለት ህወሓት ተማሪውን የሚመለከተው "ከምንም በላይ በብጥብጥ መንስኤነት" መሆኑ፤ ለዚህ መድህኒቱ ደግሞ ተማሪውን በኢህአዴግ አመራር አባላት "መያዝ" መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ይገልፃል። ቀጥሎም "በምርጫው ሊፈጠር የሚችለውን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሁከትና ብጥብጥ ለማስቆም በማደራጀት መረጃ ለመጥለፍ አመችነቱ የላቀ እንደሚሆን ታምኖበታል" በማለት መረጃ መጥለፍ የዩኒቨርስቲዎችና የትምህርት ሚኒስቴር ሥራ እንደሆነ አድርጎ ያቀርባል።

የማንዋሉን ዓላማዎች በሚገልፀው ክፍል ደግም "... የከፍተኛ ትምህርት የትምህርት የልማት ሰራዊት ግንባታን ወይም የፓለቲካ ሰራዊት ግንባታ በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተደራጀና በተናቀጀ ሁኔታ በማቀጣጠልና በማስቀጠል ... ምርጫ 2007 ውጤታማ ለማድረግ እና የኢህአዴግን አሸናፊነት ለማረጋገጥ ነው" በማለት ተቋማቱን የኢህአዴግ የምርጫ መሣሪያ መሆናቸውን፤ ግባቸውም የኢህአዴግ አሸናፊነትን ማረጋገጥ መሆኑ ይገልፃል።

በገጽ 3 ላይ ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች "በኢህአዴግ ላይ ያላቸው አቋም የወረደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በማንኛውም ተቃውሞ ድምፅ ከተጠሩ፤ ሰልፍ የሚያደምቁ፤ ተቃውሞን ከግብ ለማድረስ ሁነኛ መሳሪያ ናቸው። ተማሪዎች በየትኛውም ሐገር እንደታየው አደባባይን የመያዝ ህዝብን አስተባብረው ለተቃውሞ የማሳደም እድላቸው የሰፋ በመሆኑ ከዚህም ሲያልፍ፤ የኢህአዴግ ምከታን በመቃወም ለጠላት ጎራ ተሰልፈው የመታጠቅ እድላቸው ከፍተኛ ነው" ሲል "በወጣቱ እጠላለሁ" የሚለው የህወሓት/ኢህአዴግን ስጋት አፍረጥርጦ ያወጣል። ትንሽ ወረድ ብሎ ደግሞ "በተለይ በአሁኑ ሰዓት ፈተና ላይ የጣለን የምርጫ ጉዳይ እንደምናሸንፍ ቃል የተያዘለት ቢሆንም፤ ፈተናዎች የሚፈጠሩት በህዝብ እና በራሱ ታማኝ ባልሆኑ ሃይሎች ማለትም በመንግስት ክንፍ አይቀለበስም ብሎ ማሰብ አይቻልም። በዚህም ቀድሞ መዘጋጀት ያለበት እና ለሁከት እና ለብጥብጥ መሳሪያ ሊሆን የሚችለው የህዝብ ክንፍ የተማረው ሃይል ሊሆን ስለሚችል ሊታሰብበት ይገባል" ሲል በተማረው ወጣትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሠራተኞች ላይ ያለው ጥርጣሬና ፍርሃት ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ይገልፃል።

የ2007 ምርጫ በህወሓት ሹማምንት ላይ የፈጠረውን ጭንቀት በዚህ ሰነድ ላይ በገሀድ የሚታይ በመሆኑ እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በጥንቃቄ ሊነበብና ሊተነተን የሚገባው ነው። ለምሳሌ በገጽ 6 ላይ ስለዩኒቨርስቲ ተማሪ ሲገልጽ "የአመፅ እና የብጥብጥ መነሻ ሊሆን የሚችል ሀይል መሆኑን በአክራሪዎች ሲጠለፍ፤ ከመንግስት ሃይማኖቱን እየመረጠ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፤ በጅማ ዩኒቨርስቲ፤ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ እና በሌሎችም ትምህርቱን ትቶ ሲኮበልል ተመልክተናል" ይላል። ለተማሪዎች፣ ከመንግሥት እና ከሃይማኖት አንዱን እንዲመርጡ ተደርጎ ሃይማኖታቸውን የመረጡ መኖራቸውን እና ይህ ደግሞ አደገኛ ነገር መሆኑን ነው ይህ ዓረፍተ ነገር የሚነግረን። ለመሆኑ ይህ ምን የሚሉት ምርጫ ነው? በእንዴት ያለ ሥርዓት ነው ዜጎች ከመንግስትና ከሃይማኖት አንዱን ምረጡ የሚባለው? እንዲህ ዓይነት ምርጫ ቀርቦ ሃይማኖትን መምረጥ እንዲህ ክፉ ነገር የሆነው ለምንድነው? ይህ ጉዳይ ብቻውን ብዙ የሚያነጋግር ነገር አለው።

በገጽ 8 ላይ ደግሞ "ከፍተኛ አመራሩ ተቋማዊ ለውጥ እንዲሁም የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ ቴክኒካዊ ሳይሆን ፓለቲካዊ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝቦ ካለእርሱ ባለቤትነትና ቀጥተኛ ተሳትፎ ሰራዊት መገንባት እንደማይቻል በመገንዘብ የመሪነት ሚናውን ካለምንም ማወላዳት መወጣት ይጠበቅበታል" በማለት እየተሠራ ያለው የፓርቲ ወገንተኛ የሆነ ፓለቲካ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የትምህርት ተቋማት መሪዎች ዋና ተልዕኮ ትምህርት ማስተማር ሳይሆን የወያኔ ፖለቲካን ማስፈጸም መሆኑን ምንም ሳይጎረብጠው ፍርጥርጡን ያወጣዋል። ትንሽ ወረድ ብሎም "የጋራ መግባባት የምንለካው በመጀመሪያ ለምርጫው የኢህአዴግ የድጋፍ የድል ሰራዊት ብዛት ነው" በማለት ከላይ ያለውን በማጠናከር ወገንተኛነቱም ለኢህአዴግ መሆኑ ያውጃል። በመጨረሻም "... ሁሉም የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች ውጤታቸው የሚሞላላቸው ለምርጫው በሚያዘጋጁት የድጋፍ ሃይል ይወሰናል" በማለት የአካዳሚ ነፃነት ብቻ ሳይሆን የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓትን ለቀብር ያዘጋጃል።

ይህ ነው የህወሓት የትምህርት ፓሊሲ! የዩኒቨስቲዎች ቁጥር ለማመን በሚቸግር መጠን ቢጨምር፤ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላ በብዙ መቶኛዎች ቢያድግ ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ፓሊሲ ከተገነባ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ይገኛል የምንለው ፋይዳ ምንድነው?

ህወሓት በገሀድ በጠላትነት የፈረጃቸው የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣ መምህራንና ሠራተኞች ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ በአጽንኦት እንዲመለከቱ ግንቦት 7፣ የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያሳስባል። ትውልድንም የትምህርት ሥርዓቱንም የማዳን ግንባር ቀደም ኃላፊነት በተማሪዎችና በመምህራን የወደቀ ሸክም ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል። መላው የትምህርት ሥርዓት ለአንድ ፓርቲ የምርጫ ውድድር መሣሪያነት ሲውል ማየት እና የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች የሥራ አፈፃፀም የሚወሰነው ለገዢው ፓርቲ ባስገኙት ድምጽ ብዛት ነው መባሉ፤ እነሱም ይኸንን ተቀብለው መሥራት መቀጠላቸውን የመሰለ አሳፋሪ ነገር በአካዳሚያ ውስጥ የለም። የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን ይህን ውርደት መቀበል የለባቸውም። ሰነዱ ህወሓት ከፍተኛ ትምህርትን የሚመለከትበት ዕይታ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነውና ለምርጫ ወቅት ብቻ የተዘጋጀ የአጭር ጊዜ መመሪያ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ይህ ሰነድ ህወሓት፣ ተማሪዎችንና መምህራንን እንደጠላት፤ ተቋማቱን ደግሞ ጠላትን እንደመቆጣጠሪያ መሣሪያ እንደሚመለከት፤ ይህ ዕይታው ደግሞ ቋሚ መሆኑ በግልጽ ያሳያል። በህወሓት ዕይታ ከተገነቡ ተቋማት ምን ዓይነት ትምህርት ይገኛል?

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት ኃላፊዎችና ፕሬዚዳንቶች ሆይ! ለገዛ ራሳችሁ ክብር፣ ለአካዳሚ ነፃነት፣ ለትውልድ ስትሉ በዚህ መመሪያ ላይ አምጹ! "እንቢ፣ አሻፈረን፣ በዚህ መመሪያ አንገዛም" በሉ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎናችሁ ይቆማል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

## የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር በመስቀል አደባባይ ለጠራዉ የአዳር ተቃዉሞ የእውቅና ጥያቄ አቀረበ

በቅርቡ ተቋቁሞ ስራዉን የጀመረዉ የዘጠኙ ፓርቲዎች ትብብር አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ዉስጥ ህዳር 18 ቀን የአዳር ተቃዉሞ ስልፍ ማድረግ እንዲችል ለመስተዳድሩ የእዉቅና ጥያቄ ማስገባቱን የትብብሩ የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ አሳወቀ። የእውቅና ደብዳቤውን ኢንጅነር ይልቃል ጌትነት የሰማያዊ ፓርቲና የትብብሩ ሊቀመንበር፣ የከንባታ ህዝቦች ሊቀመንበርና የትብብብሩ ም/ሊቀመንበር አቶ ኤርሚፎ ኤርጌሎ፣ አቶ ግርማ በቀለ ከኦሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅትና የትብብሩ ፀኃፊ እና የመኢዴፓ ሊቀመንበርና የትብብሩ ገንዘብ ያዥ አቶ ኑሪ ሙደሲር በጋራ ማስገባታቸውን ነገረ ኢትዮጵያ ዘግቧል።

የትብብሩ አመራሮች ወደ መስተዳድሩ በሄዱበት ወቅት የአቶ ማርቆስ ተወካይ ለሆኑት አቶ ፈለቀ አበበ ደብዳቤውን ለመስጠት ጥረት ማድረጋቸውንና ‹‹የከንቲባ ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አሰግድ ጌታቸው የለም፣ እሱ ካልመራበት መቀበል አንችልም›› በሚል ደብዳቤውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የገለጸው ነገረ ኢትዮጵያ፣ የትብብሩ አመራሮች ታመዋል በተባሉት በአቶ ማርቆስ ተወካይ በአቶ ፈለቀ ቢሮ በአራት ምስክሮች ፊት ደብዳቤውን ማስቀመጣቸውን ዘግቧል። አመራሮቹ በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በፈጣን መልዕክት መላካቸውንም ጋዜጣው ዘግቧል። ለአንድ ቀንና ሌሊት የሚካሄደው ተቃውሞ ህዳር 27 ከጠዋቱ 3 ሰዓት ተጀምሮ ህዳር 28 ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ እንደሚጠናቀቅ ለማወቅ ተችሏል።

## ለሀገር ነጻነት የወጣቱ ተሳትፎ ቀጣይነት ይኑረው!

ከ1997 ምርጫ ማግስት ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጣቶችና በሁሉም የእድሜ ክልል የሚገኙ ዜጎች ለሀገራቸው የዲሞክራሲ መብት መከበር እያደረጉት ያለው አስተዋጽኦ ላቅ እያለ መምጣቱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ይህን ተከትሎ ዛሬ ወጣቱ የወላጆቻችን ደምጽ ይከበር፣ ኢትዮጵያዊነት በዘረኝነት አይፈተንም! ነጻነት ዳቦ አይደለም! እስራትና ግድያ በኢትዮጵያ ይቁም! የወያኔ አገዛዝ በቃን! በሚሉ በበርካታ ወጣቶች ጩኸት የወያኔ ሹማምንትና አገልጋዮቹ ላይ የፈጠረው ድንጋጤ ወጣቱን ሽብርተኛ አስደርጎታል።

ወጣቶች ህዝብን አስተባብረው ለተቃውሞ በማሳደም የወያኔን ዘረኝነት በመቃወም ረገድ የተለያዩ ዘዴዎችን ከሌሎች የነጻነት አቢዎት እንቅስቃሴ በመማር እምቢተኝነትን በማሳየት ጅማሮ ላይ ናቸው። ሰሞኑን በባህርዳር ከተማ የተጀመረው የእምቢተኝነት ዘመቻ በሚቀጥለው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ይቀጣጠል ዘንድ ወጣቱ ሃላፊነት አለበት። ሀገራችን መስቀለኛ መንገድ ላይ ነች። ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው መራራ ትግል ውስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርበታል። አባቶቻችን የውጪ ሀገራትን ወራሪዎች ወራራ ለመመከት ሁሉም ሰው የሚችለውን ሁሉ እንዲያደርግ ያደረጉት ጥሪ አሁንም ላይ ይሰራል።

ለራሳችን ክብር፣ አንድነት፣ ለሀገር ነጻነትና ህልውና መከበር ኢትዮጵያዊ እምቢተኝነት የሚጀምረው ከትንሽ ነው። ህወሃት በጠላትነት የፈረጃችሁ የዛሬ ወጣቶች የሆናችሁ ዘመን በሚፈቅድላችሁ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በመላው ሀገሪቱ ወረቀት ከመበትን አንስቶ ሌሎች ይትግል ስልቶችን ተጠቀሙ። ኢትዮጵያ ሀገራችሁ በአንድ ጠባብ ዘረኛ ቡድን መዳፍ ውስጥ ማልቀስ ከጀመረች ሰነባብታለች። ዜጎቿ የግለሰብም ሆነ የቡድን መብታቸው ተረግጦ በባርነት እየተገዙ ነው። ጉልበታቸውና ሀብታቸው እየተመዘበረ ሲሆን፤ ለነጻነት፣ ለዲምክራሲና ለፍትህ የጮኹ ሁሉ ሽብርተኛ ተብለው ወደ ማጎሪያ እየተወረወሩ ነው።

ስለዚ ህ ስለ ሀገራችን፣ ስለራሳችን የግልም ሆነ የቡድን ጥቅም ስንል በሀገሪቱ የትኛውም ክፍል የተጀመረውን የእምቢ አልገዛም ባይነት እንቅስቃሴ እንደግፍ፣ እንሳተፍ! በባህርዳር የተጀመረውን የወጣቶች እንቅስቃሴን አድንቀን ይህ ተነሳሽነት በሌላውም የሀገሪቱ ክፍል መቀጠል ያለበት ነው።

ይህን በማድረግ ወደ ትግሉ በመቀላቀል ካልተሳተፍን በስተቀር ትግላችን አንድ እርምጃ ወደፊት ፈቀቅ ማድረግ እንደማንችል ግንቦት 7 ያምናል። ስለሆነም ሁሉም አካላት በያለበት በየሚኖርበት፣ በሚችለው አቅሙ ሁሉ ወደትግሉ በንቃት ተሳተፍ! አብረን ታግለን ነጻነታችንን እናረጋግጥ! ለኢትዮጵያ ትንሳኤ፣ የነጻነት አዋጆች ነጋሪ፣ አብሳሪ ትውልዶች እንሆን ዘንድ ሳንታክት እንታገል ዘንድ ወቅቱ የሚጠይቀው ጥሪ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## የኢህአዴግን ፎርም አንሞላም አባልም አንሆንም ያሉ ተማሪዎች ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው

በአዊ ዞን አንከሻ ወረዳ ውስጥ የሚማሩ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች የኢህአዴግን የአባልነት መሙያ ፎርም ወስደው እንዲመዘገቡ በርእሰ መምህራቸው አማካኝነት ቢጠየቁም፣ ከ700 ያላነሱ ተማሪዎች ድርጊቱን ተቃውመዋል። ተማሪዎቹ የአባልነት ቅጹን በሁለት ቀናት ውስጥ የማይሞሉ ከሆነ ከትምህርት ቤት እንደሚባረሩና ለፈተናም እንደማይቀርቡ ተነግሯቸዋል። “ከእንግዲህ ኢህአዴግ የሚባል ነገር ማየት አንፈልግም” ያሉት ተማሪዎች ፣ በትምህርት ቤት አስተዳደሪዎች የቀረበላቸውን ውትወታ ውድቅ አድርገዋል።

ምንም እንኳ አንዳንድ ተማሪዎች በስጋት የአባልነት ፎርም ቢሞሉም አብዛኛው ተማሪ ግን ጥሎ መውጣቱን ከአካባቢው ያገኘነው መረጃ አመልክቷል። ጉዳዩን በማስመልከት ጥያቄ ያቀረብንላቸው የመኢአድ ምክት ሃለፊ አቶ ዘሪሁን ባንቲ፣ ተማሪዎች በሁለት ቀናት ውስጥ ፎርም የማይሞሉ ከሆነ ከትምህርት ገበታቸው እንደሚባረሩ ገልጸው፣ መንግስት በአቋሙ ከጸና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ ይችላሉ ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል። በአካባቢው በተቃዋሚዎች ላይ እየደረሰ ያለው መዋከብ መጨመሩን የገለጹት አቶ ዘሪሁን፣ የእርሳቸው ልጅ የተቃዋሚ አባል ልጅ ናት በሚል ሰኞ እለት ከትምህርት ቤት ስትመለስ በአንድ የካደሬ ልጅ ተደብድባ ወደ ህክምና መወሰዱዋን ገልጸዋል። በጉዳዩ ዙሪያ የወረዳውን ባለስልጣናት ለማነጋገር ያደረግነው ሙከራ አልተሰካም።

ኢህአዴግ የሁለተኛ እና ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን አስገድዶ አባል ለማድረግ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ በተጨማሪ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችም የአባልነት ፎርም እንደሚሉ እንቅስቃሴ ጀምሯል። እድሜያቸው ከ12 አመት በታች የሆኑ ተማሪዎች ” ታዳጊ የኢህአዴግ አባል” ተብለው ይመዘገባሉ። ኢህአዴግ በመላ አገሪቱ 6 ሚሊዮን አባላት እንዳሉት ይገልጻል። ይሁን እንጅ አብዛኞቹ ድርጅቱን ለጥቅምና ለህልውና ብለው የሚቀላቀሉ በመሆኑ፣ ለኢህአዴግ ህልውና ስጋት መፍጠራቸውን አቶ አዲሱ ለገሰ ለድርጅቱ አመራሮች በጻፉት ወረቀት ላይ ገልጸዋል። ኢህአዴግ ነባር አባላቱን በሁለተኛ ደረጃና በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ለመተካት ቢያስብም አብዛኛው ተማሪ ኢህአዴግን መጥላቱ እቅዱ ሊሳካ እንደማይችል የድርጅቱ አባላት ይናገራሉ። የትምህርት ሚኒስቴር ሰሞኑን ለኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮች ባዘጋጀው የትምህርት ሰራዊት ግንባታ ወረቅት ላይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በኢህአዴግ ላይ ጥላቻ እንዳላቸው ማተቱን መዘገባችን ይታወሳል።

## የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን ለማክበር መንግስት ከፍተኛ ወጪ መደበ

በየአመቱ ህዳር 29 ቀን ወያኔ የኢትዮጵያን የተለያዩ ብሔረሰቦች በቀለማቀለም ያሸበረቀ ልብስ እያለበሰ እኩልነታችሁ ተከበረ እያለ የሚቀልድበትን ቀን ዘንድሮም ለማክበር ሽርጉዱን መጀመሩንና የሰዉ ልጅ እየተራበ በሚሞትበት አገር በዓሉን ለማክበር ብቻ ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት አንደተመደበ ለማወቅ ተችሏል።ለዝግጅት ክፍላችን የደረሱ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ዝግጅቱን ከማቀድ ጀምሮ የተለያዩ ስራዎችን የሚፈጽሙት ከህወሃት ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች ናቸው። በኢትዮጵያ የሚከበሩ በአላትን እነዚህ ተቋማት ያለተቀናቃኝ በመውሰድ እየበለጸጉበት መሆኑን ምንጮች ይናገራሉ።

የዘንድሮዉን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በዐል አከባበር አስመልክቶ ከወያኔ/ ኢህአዴግ ጸሀፈት ቤት የወጣው መረሃ ግብር እንደሚያመለክተው የዘንድሮው በአል መሪ ቃሎች ህብረ-ብሄራዊ አንድነታችን ለህዳሴያችን፣ ህገመንግስታችን የህዳሴያችን የማእዘን ድንጋይ ነው፣ ህገመንግስት እና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ማክበርና መስከበር የእያንዳንዱ ዜጋ ሃላፊነት ነው፣ የመለስ ሌጋሲን ጨብጠን የኢትዮጵያን ህዳሴ እውን እናደርጋለን የሚሉ መለእክቶች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

## በሰሜን የአገሪቱ ክፍል ከፍተኛ ወታደራዊ እንቅስቃሴ እየታከሄደ ነው

የተቃዉሞ ድምጽ በሰማ ቁጥር እንደ በቅሎ የሚደነብረዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የሰሜን ኢትዮጵያን የተለያዩ አካባቢዎች በወታደርና በከባድ መሳሪያዎች ለማጠር ባወጣዉ ዕቅድ መሠረት ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ሠራዊት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መጓጓዝ መጀመሩን ከወደ ሰሜን ኢትዮጵያ በየቀኑ የሚደርሱን መረጃዎች ያስረዳሉ። የወያኔ አገዛዝ ወታደራዊ እንቅስቃሴዉን በጸጥታ ማስከበር ስም ለመሸፋፈን ቢሞክርም የሰሞኑ ወታደርና መሳሪያ ማጓጓዝ የተጀመረዉ ወያኔን በሃይል አስገድደው ለማውረድ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ጥቃት ሊሰነዝሩ ይችላሉ የሚለው ስጋት እያየለ በምጣቱ ሳይሆን እንደማይቀር ብዙ ታዛቢዎችና አካባቢዉን በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖች ይገምታሉ።

በአካባቢው ያለው የጸጥታሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆ መሄድ ገዢውን ፓርቲ እንዳሳሰበው የሚናገሩት እነዚሁ ምንጮች አክለዉ እንደተናገሩት፣ በተለይም በጠረፍ አካባቢ የሚኖረው ወጣት የተቃዋሚ ሃይሎችን ድንበር እያቋረጠ በስፋት እየተቀላቀለ በመሆኑ፣ ወያኔ ሃይሉን በድንበር አካባቢ እንዲያጠናክርና ከፍተኛ ቁጥጥር ለማድረግ ሳያስነሳሳው እንዳልቀረ ይናገራሉ። ለሉዓላዊነትና ለአገር አንድነት ምንም ደንታ የሌለዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት መከበር የሚታገሉ ኃይሎችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር እንዲያስችለዉ ከሱዳን ጋር ወታደራዊ ዉሎችን መፈረሙ የሚታወስ ሲሆን በዚህ ስምምነት መሰረት ወያኔ የተወሰነ ጦሩን ወደ ሱዳን በማስገባት ፀረ ህዝብ፤ ፀረ አገርና ፀረ ነፃነት እንቅስቃሴ መጀመሩ የሚታወስ ነዉ።

## በአማራ ክልል ቅርሶች በከፍተኛ ሁኔታ እየዘረፉ ከሐገር እየወጡ ነው

በአማራ ክልል የደቡብ ወሎና የሰሜን ሸዋ ዞን ወረዳዎችና አብያተክርስቲያናት ተገቢ ጥበቃ ባለማግኘታቸው የተለያዩ ቅርሶች የተዘረፉና የጠፉ መሆኑን የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ በአመት አንድ ጊዜ በሚዘጋጀው የቅርስ ጉባኤ ላይ ገለጸ። በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በተለያዩ ወረዳዎች 37 ቅርሶች መሰረቃቸውን ይፋ ያደረጉት የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ አቶ አለበል ደሴ፣ በክልሉ ከ2001 በጀት ዓመት ጀምሮ እስከ 2006 መጨረሻ ባለው ጊዜ የተዘረፉ ቅርሶች 124 መድረሳቸውን ተናግረዋል።

በክልሉ ብቸኛ የሆነው የደሴ ሙዙየም በስተደቡብ አቅጣጫ ጫካ በመሆኑና ዙሪያውም ምንም ዓይነት አጥር ስለሌለውየጥበቃ ቢሮው ተሰብሮ በውስጡ የነበሩ ሁለቱም የጦር መሣሪያዎች ከነሙሉ ጥይታቸው ከመሰረቃቸውም በላይ እስከአሁንም አለመገኘታቸውን ገልጸዋል። ቅርሶች በመስታውት ዉስጥ ተቆልፈው ስላልተያዙ ለአቧራና ለአላስፈጊ ንክኪ መጋለጣቸውም ሃላፊው ተናግረዋል።

በሰሜን ሸዋ ዞን ባሉ የተለያዩ ወረዳዎች በሚገኙ ጥንታዊ አብያተክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶች ተገቢውን ጥበቃ ባለማግኘታቸው በሌቦች መሰረቃቸውንና አብዛኞዎቹ አለመገኘታቸውን በውይይቱ ላይ የተወሳ ሲሆን የአንኮበር ማሪያም ቤተክርስቲያን 3 የብር መቋሚያዎችና 7 የብር ጻናፅልች፤ በአንፆኪያ ወረዳ በ03 ቀበሌ አጥቆ በዓታ ማሪያም ቤተክርስቲያን 9 የብራና መጽሃፍት፣ 3 ሌሎች የመገልገያ መጽሃፌት እና 1 የመፆር የነሃስ መስቀል ተሰርቀው እስካሁን አልተገኙም።በሞረትና ጅሩ ወረዳ የሚገኘው ይማደጋ ቅደስ ሚካኤሌ ቤተክርስቲያን ውስጥ ዘራፉዎች ገብተው 2 የቅዱስ ሚካኤል ጽላት ፣ 1 የመስቀለ እየሱስ ጽላት፣ 3 የነሃስ የመፆር መስቀል፣ 1 መጎናፀፉያ የተዘረፉ መሆኑ ለአብነት በውይይቱ ላይ ተነስቷል። በቅርስ ዘረፋው የባለስልጣናት እጅ አለበት ሲሉ ሃሳብ ያነሱት ተወያዮች እንዴት በህገወጥ የሰዎች ዝውውር የተሳተፉ ባለስልጣናት ቅርስ ዘረፋን ይከላከላሉ ተብሎ እንዴት ይገመታል ሲሉ ሞግተዋል።

በጋይንት አካባቢ ብቻ ከ30 ያላነሱ አብያተክርስቲያናት ቅርሶች መዘረፋቸውን ጥቆማ እንደደረሰው የክልሉም ሆነ የፌደራል ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ሚኒስቴር ቢያሳዉቅም ጉዳዩ ተጣርቶ የተወሰደ እርምጃ የለም። በአማራ ክልል የሚገኙ የቅርስ መገኛ ተቋማት 3ሺ እንደሚደርሱ ቢገመትም ሙዙየም በማሰራት ቅርሶቻቸውን በጥንቃቄ ለእይታ እያቀረቡ ያሉት ግን 13 ብቻ ናቸው።በሌላ በኩል ደግሞ በብሄራዊ ሙዚየም ውስጥ ይገኙ የነበሩ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚዘክሩ መጽሃፍት በተቀነባበረ መልኩ በርካሽ ዋጋ ለነጋዴዎች የተሸጡ መሆናቸው የተዘገበ ሲሆን፣ እስካሁን ለኢሳት በደረሰው መረጃ የጆብ ሎድፍ 1664፣ 1700፣ 1800፣ የጀምስ ብሩስ፣ የካርሎ ሮሲኒ፣ በጣሊያን ወረራ ጊዜ ይታተሙ የነበሩ የቄሳር መንግስትና የሮማ ብርሃን የተባሉ ጋዜጦች፣ 2 ሺ ኪሎ ግራም ይመዝናሉ የተባሉ የአጼ ቴዎድሮስ፣ የአጼ ዮሃንስና የአጼ ሚኒሊክ ደብዳቤዎች ተቸብችበዋል።

## የሐረሪ ክልል ፕሬዚዳንት በክልሉ ፓርቲ ዋና ጸሃፊ መደብደባቸዉ ተሰማ

ባለፈው አርብህዳር 12፣ 2007 ዓም የሃረሪ ክልል ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ሙራድ አብዱላሂ በሀረሪ ሊግ ዋና ጸሃፊና በንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሃለፊ አቶ ነቢል መሃዲ ጽ/ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ መደብደባቸዉን ምስራቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። በዚህ የወያኔ ባለስልጣናት ትክክለኛ መገለጫ በሆነዉ አተካሮ፤ስድብና ቡጢ በተቀላቀለበት ግብግብ በተደብዳቢዎቹ ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰ ለግዜዉ ባይታወቅም ሁኔታዉ የክልሉን ባለስልጣናት ለሁለት መከፈሉንና በክልሉ የጸጥታ ስጋት መፍተረሩንም  ምንጮቻችን በላኩልን ዜና አክለዉ ተናግረዋል።በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው አቶ ነቢል መሃዲ ከወራት በፊት በተደረገ ግምገማ ከሀረሪ ሊግ ዋና ጸሃፊ እንዲነሱ ከተደረጉ በሁዋላ፣ ዘግይቶ ደግሞ ከንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ሃላፊነታቸው ተነስተው በክልሉ እቃ ግዢ ውስጥ በሃላፊነት እንዲሰሩ በፕሬዚዳንቱ ታዘዋል። ፕሬዚዳንቱ ተቀናቃኞቻቸውን በሰበብ አስባቡ እያስወገዱና ስልጣኑን በዘመዶቻቸው እያስያዙ ነው ብለው የሚያምኑ ሌሎች የፓርቲው አመራሮች ፕሬዚዳንቱን ሲቃወሙና ፕሬዚዳንቱ ሰሩዋቸው የሚሉዋቸውን ስራዎች ለአደባባይ እያበቁ ነው። የፕሬዚዳንቱ ባለቤት በቅርቡ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይዘው አሜሪካ መግባታቸው ፕሬዚዳንቱ በባልደረቦቻቸው እንዲናቁ እንዳደረጋቸው የሚናገሩት ምንጮች፣ ባለፈው አርብ የተከሰተው ድርጊቱም የንቀቱን ደረጃ የሚያሳይ መሆኑን ይገልጻሉ።

አቶ ነቢል ከፕሬዚዳንቱ ጋር ለመነጋገር እንደሚፈልጉ ጸሃፊያቸውን አስፈቅደው ከገቡ በሁዋላ፣ የፕሬዚዳንቱን አንገት በማነቅ በቦክስ መማታት ሲጀምሩ ጸሃፊዎች ተሯሩጠው ለመገላገል ሞክረዋል። በጥበቃ ላይ የነበሩት ፖሊሶች በፍጥነት ደርሰው አቶ ነቢልን ይዘው የወጡ ሲሆን፣ አቶ ነቢል ይታሰሩ አይታሰሩ በሚለው ላይ ክፍፍል መፈጠሩንም ምንጮች ገልጸዋል። ይሁን እንጅ አቶ ነቢል ይህን ዜና እስካጠናከርንበት ጊዜ ድረስ አለመታሰራቸውን ለማወቅ ተችሎአል። አቶ ነቢል የሀረሪ መዘጋጃ ቤት ሃላፊና የትምህርት ቢሮ ሃላፊ ሆነው ሰርተዋል።

በሀረሪ ክልል ባለስልጣናት መካከል የሚታየው የእርስ በርስ ሽኩቻ ክልሉን በበላይነት ለሚያስተዳድሩት ለህወሃቱ ጄ/ል አብራሃ ወ/ምርያም ፈተና እንደሆነባቸውም ምንጮች ይገልጻሉ። በተለይ ከሃረሪ ተወላጆች ውጭ ያለው አብዛኛው ህዝብ በዘር መድሎ ከፍተኛ የሰብአዊና የአስተዳደር እግሮች እየደረሰበት መሆኑ፣ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ የሚችል ውጥረት እንዲፈጠር ማድረጉን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ምንጮች ይናገራሉ። የሀረሪ ክልል 36 ቀበሌዎች ያሉት ሲሆን፣ በገጠር የሚኖረው አብዛኛው ህዝብ ኦሮምኛ ተናጋሪ ሲሆን፣ በከተማ የሚኖረው ደግሞ በአብዛኛው አማርኛ ተናጋሪ ነው። ክልሉ አደርኛና ኦሮምኛን ብቻ የስራ ቋንቋ እንዲሆን በማድረጉ በክልሉ የሚኖረው ከ65 በመቶ በላይ የሚሆነው የአማርኛና ሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ለከፍተኛ ችግር መዳረጋቸውን በተደጋጋሚ ይገልጻሉ። ምንም ሰው ማመልከቻውን በአደርኛ ወይም በኦሮምኛ ካልጻፈ ተቀባይነት እንደማያገኝ የሚገልጹት ነዋሪዎች ለአስተርጓሚ በሚል ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጡ እየተገደዱ ነው።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org